የመጀመሪያ ቀን ________________

የመጨረሻ ቀን ________________

# የሕይወቴ ጉዞ

ስም ______________________________________________________________

______________________________________________________________

በየዕለቱ መለወጥ

WWW.DAILYTRANSFORMATION.ORG

ከኢየሱስ ጋር ባለህ ጉዞ **የሕይወቴ ጉዞ**እንድትለማመድ የሚስችልህን አራት ነገሮችን ተመልከት

● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ●

## አዳምጥ፤

እግዚአብሔር ይናገራል፤ በየዕለቱም አብሮህ ሊጓዳ ይፈልጋል።በየዕለቱ ፍቅሩን ለማጣጣም እና ለማን እንድትመሰክር እንደሚፈልግ ለማወቅ በየዕለቱ መጸለይ ያለብህ ለዚህ ነው።ይህ ማስታወሻ፤በጸሎት ወደ እግዚአብሔር ልታቀርባቸው የምትፈልጋቸውን ጥያቄዎች የምትጽፍበት ክፍል አለው።እግዚአብሔር ጸሎትህን የመለሰበትን ቀን መጻፍህን አትርሳ።

## ፈልግ፤

ከእግዚአብሔር ጋር ከመገናኘትና እርሱን ለመፈለግ በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስህን አንብብ። እግዚአብሔር በሙሉ ልባችን እንድንፈልገው  ይፈልጋል፤ይህ ሲሆን፤እናገኘዋለን።በሚቀጥለው ክፍል ፤ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ኢየሱስን እና መንገዱን አንዴት እንደምንፈልግና እንደምናገኝ እናያለን።

## ህብረት፤

ኢየሱስን እንደአምላካችንና መሪያችን ስንፈልገው ቤተሰብ እንደሰጠን እንረዳለን። እርሱ አባታችን ነው፤ ተከታዮቹ ደግሞ እህትና ወንድሞቻችን ናቸው ። እግዚአብሔር የእርሱን ቤተሰብ እሴቶች ለማጠናከርና በሕይወት ውጣ ውረድ ውስጥ ስናልፍ ደግሞ ሊያበረታታን ይፈልጋል። መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብና ማጥናት የሚወዱ የኢየሱስ ተከታዮች ቡድን ፈልግ። ስትገናኙ በጋራ እንጀራ ቁረሱ። በምትሰባሰቡበት ጊዜ የተማራችሁትን የምትመዘግቡበት መመሪያዎችንና ሳምንታዊ የሕብረት ስብሰባ ገጾችን አካተናል።

## ተናገር

እግዚአብሔር ሌሎችን ወደ ቤተሰቡ እንድናመጣ ይፈልጋል።በእንክብካቤና የኢየሱስን እውነት በመናገር የእግዚአብሔርን ፍቅር ስናካፍል ሰዎች በሕይወታቸው እጅግ አስፈላጊውን ውሳኔ እንዲወስኑ እንረዳቸዋለን። ታሪካችሁን መናገር እንድትችሉ የሚረዳችሁን እና የኢየሱስን ፍቅር ያካፈላችኋቸውን ሰዎች ስም  ዝርዝር የምታሰፍሩበት ቦታ አዘጋጅተናል።



# ማዳመጥ

# ማ ዳመ ጥ፤ **ጸሎትን መለማመድ**

• • • • • • • • • • • • • •

እግዚአብሔር፤ ከእርሱ ጋር ባለን በጤናማ ግንኙነት አማ ካኝነት እያበበ የሚ ሄድ ሕብረት ከእርሱ ጋር እንዲኖረን ይፈልጋል።ጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር መነጋር ነው። እኛንና በሕይወታችን ያሉ ሰዎችን እዲረዳ መ ጠየቅንም ያካትታል።ጤናማ ግንኙነት ማዳመጥን ይጨምራል። መንፈስ ቅዱስ እንዴት እንደሚጸለይ ሊመራን ይፈልጋል።በጸሎት ርዕስ ዝርዝርህ ውስጥ ሰዎችን ይጨምራል፤ እንዴት እንደምንከተለው ም ሊመራን ይፈልጋል።አስተውል፤በየዕለቱ መንፈሳዊ ውግያ ይገጥምሃል።ሰይጣን በፈተና እና በፍርሃት ሊያሸንፍህ ይፈልጋል። ጸሎት፤ በቀን ውስጥ ሊያጋጥምህ ስላለው ማንኛውም ሁኔታ ዝግጁ ያደርግሃል።

**እንዴት እንደሚጸለይ ካለወቅህ፤ ብቻህን አይደለህም።** የኢየሱስ የቀርብ የነበሩት እንኳን በዚህ ጉዳይ እርዳታ ጠይቀዋል። በማትዮስ 6፡5-8 ኢየሱስ ስለ ታማኝነት (ቁ. 5)፣ ትህትና(ቁ. 6)፣ እና እውነተኝነት(ቁ.7-8) አስተምሯቸዋል።

እግዚአብሔርን **<u>አመስግን፤</u>** "አባታችን ሆይ፣ በሰማይ የምትኖር ስምህ ይቀደስ" (ቁ.9፤ ፊሊጲስዩስ 4፡6)

ለእርሱ **<u>ፈቃድ</u>** ራስህን ስጥ፤ "… መንግስትህ ትምጣ፤መንግስትህ ትምጣ፤ ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁም በምድር ትሁን" (ቁ. 10)

**<u>የሚያስፈልግህን</u>** ጠይቅ፤ "የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን" (ቁ. 11)

እግዚአብሔር **<u>ይቅር</u>** እንዲልህ ጠይቅ፤ "…በደላችንን ይቅር በለን"(ቁ.12)

**<u>ስለሌሎች</u>** ጸልይ፤ "እኛም ደግሞ የበደሉንን ይቅር እንደምንል" (ቁ. 12፣ 1ኛጢሞቲዎስ 2፡1)

**<u>ለጥበቃ</u>** ጸልይ፤" ከክፉም አድነን እንጂ ወደ ፈተና አታግባን" (ቁ.13)

ኢየሱስ በሐዋርያቱ አማካኝነት ያስተማረውን ……አስታውስ፤

- ዮሐንስ እንዲህ ብሎ ጽፏል… " … በዓለም ካለው ይልቅ በእናንተ ያለው ታላቅ ነውና" 1ኛ ዮሐንስ 4፡4
- ሐዋርያው ጳውሎስ "በተስፋ ደስ ይበላቸው ፤ በመከራ ታገሡ ፤ በጸሎት ጽኑ" ሮሜ 12፡12
- የኢየሱስ ወንድም ያዕቆብ እንዲህ ሲል ጽፏል፤ "… ነገር ግን አትለምኑምና ለእናንተ አይሆንም" ያዕቆብ 4፡2
- ጴጥሮስና ዮሐንስ እንዲህ ጸልየዋል፤ "አሁንም ጌታ ሆይ ፤ ወደ ዛቻቸው ተመልከት፤ ለመፈወስም እጅህን እጅህን ስትዘረጋ በቅዱስ ብላቴናህም በኢየሱስ ስም ምልክትና ድንቅ ሲደረግ፤ ባሪያዎችህ በፍጹም ግልጥነት ቃልህን እንዲናገሩ ስጣቸው" ( ሐዋርያት ሥራ 4፡29-30)

**ቀጥሎ ያለውን የጸሎትና የመልስ ገጽ ተመልከት።** በቀንህ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ እንድትጸልይላቸው ሰዎችን ወደ ልብህ ሲያመጣ አስተውለህ አዳምጥ።ከእግዚአብሔር ጋር የጽሞና ጊዜ እያሳለፍክ እያለ ወይም ደግሞ ሰውየውን ስታየው ሊሆን ይችላል ሽክም የሚሰማህ። መንፈስ ቅዱስ እንደመራህ ከተሰማህ ወደ ሰውየው ሄደህ ልትጸልይለት እንደምትፈልግ ንገረው።የጸሎት ርዕስህንና የተመለሰበትን ቀን መዝግብ፡ ፡ በማንኛውም ሰዓት ማስተወሻህን መጠቀም እንድትችል በሄድክበት ቦታ ሁሉ ይዘኸው እንድትንቀሳቀስ እናበረታታሃለን።

# የጸሎት ርዕስ እና መልስ

| ቀን | የጸሎት ርዕስ | መልስ |
| --- | --- | --- |

DAILY TRANSFORMATION DT DAILY TRANSFORMATION



# መፈለግ

# መፈለግ፤ በየእለቱ ማንበብና መጻፍ ተለማመድ

• • • • • • • • • • • • • •

መጽሐፍ ቅዱስ የምናነበው በየዕለቱ የሕይወት መመሪያ ለመቀበል ብቻ ሳይሆን እዚአብሔር በእውነት እንድናውቀው ስለሚፈልግ ነው።መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብ ከእግዚአብሔር ጋር ጊዜ ማሳለፍ ማለት ነው፡ ፡ ፈልገው።መጽሐፍ ቅዱስ በምታነብበት ወቅት የእግዚአብሔር መንፈስ ምን እንደሚል አዳምጥ።ኢየሱስ እንዲህ ሲል ጸለየ፤ “እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንህ አንተን የላከውንም ኢየሱስ ክርስቶን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት” ዮሐንስ 17፡3 በዚህ ክፍል “ማወቅ” የሚለው ቃል **የጋብቻ አብሮነትን** የሚያመላክት ነው።እዚአብሔርን በጥልቀት ማወቅ ትችላለህ።

በማስታወሻህ እንድታሰፍር እግዚአብሔር የሚገልጥልህ ነገር ለሌሎችም ይተርፋል።ቀጥሎ፤ የማስታወሻ አያያዝን ብቻ ሳይሆን እግዚአብሐየርን የሚናገርህን እንዴት በፍጥነት እንደምታውቅ እናያለን።

### ማውጫ

ማ ስታወሻህን በም ትመ ለከትበት ጊዜ መጀመሪያ አካባቢ እንደ ማውጫ የሚያገለግሉ 4 ገጾች አሉ። የማስታወሻ መግቢያህን ከጻፍክ በኋላ በየዕለቱ ማወጫውን ትሞላለህ።

## የየዕለት ማስታወሻ ገጾች

ይህ ገጽ ፤ በግርጌ የሰፈረውን የመጽሐፍ ቅዱስ ማንበብያ መርሃ ግብር ካነበብክ በኋላ ማታወሻ የምትይዝበት ቦታ ነው።፤አንዚህ ገጾች ቁጥር መስጠት ይኖርብሃል።

## መጽሐፍ ቅዱስ የማንበብያ መርሃ ግብር

የመጽሐፍ ቅዱስ ማንበብያ መርሃግብርን መከተል፤ ለተጠያቂነት ፣ራስን ለመግዛትና ቃሉ የሚናገረውን በአግባቡ ለማወቅ ይረዳል። ይህንን መርሃ ግብር በታማኝነት ከተከተልክ፤ በዓመት ውስጥ ብሉይ ኪዳንን አንድ ጊዜ አዲስ ኪዳንን ደግሞ ሁለት ጊዜ ማንበብ ትችላለህ። የማንበብያ እቅድ፤ የምትወደውን ስድስት የመጸሐፍ ቅዱስ ክፍል ብቻ ደጋግመህ ከማንበብ ይጠብቅሃል። መጽሐፍ ቅዱስ 66 መጽሐፍ ያለው እንደመሆኑ የተወሰነውን ብቻ በማንበብ  እግዚእብሔር ሊናገርህ ከሚፈልገው  ነገር ውስጥ 90%ን ታጣለህ ማለት ነው።

# የየዕለት መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብያ እና የማስታወሻ አጠቃቀም

**1ኛ፤** መንፈስ ቅዱስ እንዲያስተምርህ እና ኢየሱስን እንዲገልጥልህ ጸልይ።ኢየሱስ ስለመንፈስ ቅዱስ እንዲህ ብሏል፤"እርሱም መጥቶ ስለ ኃጥያት ስለ ጽድቅም ስለ ፍርድም ዓለምን ይወቅሳል፤" ዮሐንስ 16፡8

**2ኛ፤** የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶቹን አንብብ፤ እያነበብክ ጌታ አንድታደርገው በልብህ ያከበደውን ቃል አስምርበት።በተከፈተ ልብ ስታነብ ፤ ጌታ የሚያበረታታ ፣ የምሪት ወይም ደግሞ የተግሳጽ ቃል ሊሰጥህ ይችላል።(2ጢሞ 3፡16)

**3ኛ፤** ንባብህን ከጨረስክ በኋላ በአዲስ ገጽ እግዚአብሔር ያስተማረህን ነገር ጻፍ፤

- ቀን
- ርዕስ
- የተማርከውን ነገር የሚገልጽ ጠቅለል ያለ ርዕስ ስጥ
- እግዚአብሔር ያስተማረህን በሚከተለው አግባብ አስቀምጠው (ለበለጠ መረጃ ገጽ 1ን ተመልከት)

DAILY TRANSFORMATION




............................... ዋናውን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ መዝግብ

**ልከታ**........................ በጥቅሶቹ ውስጥ ያየኸውን ሁኔታ መዝግብ

**በራ**......................... አሁን ያነበብከው ቃል የዛሬ ውሎህን በምን መልኩ እንደሚለውጥ ግለጽ.

**ት**.......................... የተማርከውን ለመኖር ቃል የመግባትና እርዳታ የመጠየቅ ጸሎትህን አስፍር

(በሚቀጥለው ገጽ የማስታወሻ አያያዝ ምሳሌ ተመልከት)

# የየዕለት መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብያ እና የማስታወሻ አጠቃቀም

•••••••••••••••

| 4/23 | "ተስፋን ማካፈል" | 1 |
| --- | --- | --- |
| ቀን | ርዕስ | ገጽ |

**• ቃል**

ኢየሱስ- "በጨለማ የምነግራችሁን በብርሃን ተናገሩ፤ በጆሮም የምትሰሙትን በሰገነት ላይ ስበኩ።" ማትዮስ 10፡27

**• ምልከታ**

የዓለማት ሁሉ ፈጣሪ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ለመነጋገር መፈለጉ ያስደንቀኛል። ያለ ምክንያት ግን አይመስለኝም። የሚነግረንን እንድናካፍል ነው። ኢየሱስ ሰዎችን መፍራት እንደሌለብን ይነግረናል። እግዚአብሔርን ብቻ መፍራት፤ እግዚአብሔር አባታችን ነው። ማናችንም እንድንጠፋ አይፈልግም። ስለዚህ፤ ሰዎችን አትፍሩ።

**• ተግባር**

እግዚአብሔርን እየሰማሁ ነው? ካልሆነ ፤ ከእርሱ ጋር ለብቻዬ ጊዜ እያሳለፍኩ አይደለም ማለት ነው። በጣም ባተሌ መሆኔን መናዘዝ አለብኝ። ቤቴ ጸጥ ሲል፤ በጸሎትና የሚወደኝና የሰማዩን አባቴን በማዳመጥ የጽሞና ጊዜ መውሰድ አለብኝ። በዙሪያዬ ያሉትን የምባርክበት መልዕክት እርሱ ይስጠኝ። ደግሞም ሳካፍል ሰው ባይሰማኝ እንኳን በጽናት ማካፈሌን እንድቀጥል ብርታቱን ይስጠኝ።

**• ጸሎት**

ኢየሱሴ፤ ቃልህን ሳነብና ስጸልይ ካንተ መስማት እንድችል እርዳኝ። ዛሬ ጨለማ ውስጥ እንዳለሁ ቢሰማኝም አንተን ለመስማት በፊትህ በጸጥታ እሆናለሁ። ለቤተሰቦቼ እና አብረውኝ ለሚሰሩ ተስፋን አካፍል ዘንድ ብርሃንህን ስጠኝ። በኢየሱስ ስም ጸለይኩ አሜን!

ዛሬ ባነበብኩት ቃል ምክንያት ውሎዬ እንዴት የተለየ ይሆናል?

# የየዕለት መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብያ እና የማስታወሻ አጠቃቀም

•••••••••••••••

**4ኛ፡** ወደ ማውጫ ተመልሰህ ቀን፣ ቃል፣ ርዕስና ገጽ አስገባ.

## ማውጫ

•••••••••••••••

| ቀን | ቃል | ርዕስ | ገጽ |
|---|---|---|---|
| 23/04 | ማትዮስ 10፡27 | ተስፋን ማካፈል | 1 |
| 24/04 | መዝሙር 109፡21 | እግዚአብሔር ከጠላቶቼ ይጠብቀኛል | 2 |
| 25/04 | 1ዜና 10፡13 | የኃጥያቴ ውጤት በምድር ላይ | 3 |

**5ኛ፡፡ ወደ ጸሎት ርዕሰህ ተመልሰህ ለራስህና ለሌሎች በመማለድ የዕለቱን የጽሞና ጊዜ አጠናቅ፡፡**

**አስታውስ፤** የሕይወቴ ማስታወሻ፤ ከኢየሱስ ጋር ባለህ ግንኙነት እንድታድግ እንዲረዳህ የተዘጋጀ ነው፡፡ አጠቃቀሙን እንደሚመችህ ልታስተካክለው ትችላለህ፡፡ ነገር ግን በየዕለቱ ከጌታ ጋር ጊዜ የማሳለፍ ልምድ ማዳበርህን እርግጠኛ ሁን፡፡

አንዳንዶች፤ ከእግዚአብሔር ጋር የጥሞና ጊዜ ለማሳለፍ ተመራጩ ሰዓት የቱ ነው ብለው ይጠይቃሉ፡፡ መልሱ፤ የአንተ ምርጡ ሰዓት የሚል ነው፡፡ የጠዋት ሰው ከሆንክ፤ የጽሞና ጊዜህን በጠዋት አድርግ፡፡ ንቁ የምትሆነው ከሰዓት በኋላ ከሆነ፤ በዚያ ሰዓት አድርግ፡፡ ዋናው ነጥብ፤ ኢየሱስ ምርጡን ጊዜህን ይፈልጋል፤ የቀንህን ምርጡን ሰዓት ስጠው!

# ማውጫ

| ቀን | ቃል | ርዕስ | ገጽ |
|---|---|---|---|
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |

DAILY TRANSFORMATION DT DAILY TRANSFORMATION

# የየዕለት ማስታወሻ ገጾች

| ቀን | ርዕስ | ገጽ |
|---|---|---|

DAILY TRANSFORMATION DT DAILY TRANSFORMATION

# መጽሐፍ ቅዱስ የማንበቢያ ዕቅድ
## መጽሐፍ ቅዱስን በአንድ ዓመት

••••••••••••••••••••••••••••

## መጽሐፍ ቅዱስን በአንድ ዓመት

መስከረም
1.ዘፍጥረት 1-2 ሉቃስ 1
2.ዘፍጥረት 3-5 ሉቃስ 2
3.ዘፍጥረት 6-8 ሉቃስ 3
4.ዘፍጥረት 9-11 ሉቃስ4
5.ዘፍጥረት 12-14 ሉቃስ 5
6.ዘፍጥረት 15-17 ሉቃስ 6
7.ዘፍጥረት 18-19፣ መዝሙር 3 ሉቃስ 7
8.ዘፍጥረት 20-22 ሉቃስ 8
9.ዘፍጥረት 23-24 ሉቃስ 9
10.ዘፍጥረት 25-26፣ መዝሙር 6 ሉቃስ 10
11.ዘፍጥረት 27-28፣ መዝሙር 4 ሉቃስ 11
12.ዘፍጥረት 29-30 ሉቃስ 12
13.ዘፍጥረት 31-33 aሉቃስ 13
14.ዘፍጥረት 34-36 ሉቃስ 14
15.ዘፍጥረት 37-38፣ መዝሙር 7 ሉቃስ 15
16.ዘፍጥረት 39- 41 ሉቃስ 16
17.ዘፍጥረት 42-43፣ መዝሙር 5፣ ሉቃስ 17
18.ዘፍጥረት 44-46 ሉቃስ 18
19.ዘፍጥረት 47-48፣ መዝሙር 10፣ ሉቃስ 19
20.ዘፍጥረት 49-50፣ መዝሙር 8፣ ሉቃስ 20
21.ዘፀዓት 1-2፣ መዝሙር 88፣ ሉቃ 21
22.ዘፀዓት 3-5 ሉቃስ 22
23.ዘፀዓት 6-8 ሉቃስ 23
24.ዘፀዓት 9-11 ሉቃስ 24
25.ዘፀዓት 12-13 መዝሙር 21 ሐዋ. 1
26.ዘፀዓት 14-16 ሐዋ.ሥ. 2
27.ዘፀዓት 17-20 ሐዋ.ሥ 3
28.ዘፀዓት 21-22፣ መዝሙር 12 ሐዋ.ሥ 4
29.ዘፀዓት 23-24 መዝሙር 14 ሐዋ.ሥ 5
30.ዘፀዓት 25-27፣ ሐዋ.ሥ 6

ጥቅምት
1.ዘጸአት 30-32፡የሐዋ 8
2.ዘጸአት 33-34፡መዝ.16 የሐዋ.9
3.ዘጸአት 35-36፡የሐዋ.10
4.ዘጸአት 37-38፡መዝ19፡የሐዋ.11
5.ዘጸአት 39-40፡መዝ.15 የሐዋ.12
6.ዘሌዋውያን 1-3፡የሐዋ.13
7.ዘሌዋውያን 4-6፡የሐወ.14
8.ዘሌዋውያን 7-9፡የሐዋ.15
9.ዘሌዋውያን 10-12፡የሐዋ.16
10.ዘኬዋውያን 13-14፡የሐዋ.17
11.ዘሌዋውያን 15-17፡የሐዋ.18
12.ዘሌዋውያን 18፣19፡መዝ.13፡የሐዋ.19
13.ዘሌዋውያን 20-22፡የሐዋ.20
14.ዘሌዋውያን 23፣24፡መዝ.24፡የሐዋ.21
15.ዘሌዋውያን 25፡መዝ.25-26፡የሐዋ.22
16.ዘሌዋውያን 26፣27፡የሐዋ.23
17.ዘኅልቁ 1፣2፡የሐዋ.24
18.ዘኅልቁ 3፣4፡የሐዋ.25
19.ዘኅልቁ 5፣6፡መዝ.22፡የሐዋ.26
20.ዘኅልቁ 7፡መዝ.23፡የሐዋ.27
21.ዘኅልቁ 8፣9፡የሐዋ.28
22.ዘኅልቁ 10፣11፡መዝ.27፡ማር.1
23.ዘኅልቁ 12፣13፡መዝ.90፡ማር.2
24.ዘኅልቁ 14-16፡ማር.3
25.ዘኍልቁ 17፣18፡መዝ.29፡ማር.4
26.ዘኍልቁ 19፣20፡መዝ.28፡ማር.5
27.ዘኍልቁ 21-23፡ማር.6፤7
28.ዘኍልቁ 24-27፡1ቆሮ.13
29.መሳፍንት 9፣10፡መዝ.49፡1ቆሮ.16
30.ዘፀዓት 28-29፣ ሐዋ.ሥ 7

ሕዳር
1.ዘኅልቁ 28፣29፡ማር.8
2.ዘኍልቁ 30፣31፡ማር.9
3.ዘኍልቁ 32፣33፡ማር.10
4.ዘኍልቁ 34-36፡ማር.11
5.ዘዳግም 1፣2፡ማር.12
6.ዘዳግም 3፤4፡መዝ.36፡ማር.13
7.ዘዳግም 5፤6፡መዝ.43፡ማር.14
8.ዘዳግም 7-9፡ማር.15
9.ዘዳግም 10-12፡ማር.16
10.ዘዳግም 13-15፡ገላ.1
11.ዘዳግም 16-18፡መዝ.38፡ገላ.2

# መጽሐፍ ቅዱስ የማንበቢያ ዕቅድ

## መጽሐፍ ቅዱስን በአንድ ዓመት

•••••••••••••••••••••••••••••

## መጽሐፍ ቅዱስን በአንድ ዓመት

12.ዘዳግም 19-21፡ገላ.3
13.ዘዳግም 22-24፡ገላ.4
14.ዘዳግም 25-27 ፡ገላ.5
15.ዘዳግም 28፣29፡ገላ.6
16.ዘዳግም 30፣31፡1ቆሮ.1
17.ዘዳግም 32-34፡1ቆሮ.2
18.ኢያሱ 1፣2፡መዝ.37፡1ቆሮ.3
19.ኢያሱ 3-6፡1ቆሮ.4
20.ኢየሱ 7፣8፡መዝ.69፡1ቆሮ.5
21.ኢያሱ 9-11፡1ቆሮ.6
22.ኢያሱ 12-14፡1ቆሮ.7
23.ኢያሱ 15-17፡1ቆሮ.8
24.ኢያሱ 18-20፡1ቆሮ.9
25.ኢያሱ 21፣22፡መዝ.47፡1ቆሮ.10
26.ኢያሱ 23፣24፡መዝ.44፡1ቆሮ.11
27.መሳፍንት 1-3፡1ቆሮ.12
28.መሳፍንት 4-5፡መዝ39፣41፡1ቆሮ.13
29.መሳፍንት 6፣7፡መዝ.42፡1ቆሮ14
30.መሳፍንት 8፡መዝ.52፡1ቆሮ.15

መጽሐፍ ቅዱስ በምታነብበት ጊዜ፤ እነዚህን ተመልከት
•ስለእግዚአብሔር ምን ያስተምረኛል?
•ስለሰው ምንያተምረኛል?
•ማስወገድ ያለብኝ ኃጥያት አለ?
•መታዘዝ ያለብኝ ትዕዛዝ አለ?
WWW.DAILYTRANSFORMATION.ORG

ታህሳስ
1.መሳፍንት 11፣12፡መዝ.50፡2ቆሮ.1
2.መሳፍንት 13-16፡2ቆሮ.2
3.መሳፍንት 17፣18፡መዝ.89፡2ቆሮ.3
4.መሳፍንት 19-21፡2ቆሮ.4
5.ሩት 1፣2፡መዝ.53፣61፡2ቆሮ.5
6.ሩት 3፣4፡መዝ.64፣65፡2ቆሮ.6
7.1ሳሙ 1፤2፡መዝ.66፡2ቆሮ.7
8.1ሳሙ 3-5፡መዝ.77፡2ቆሮ.8
9.1ሳሙ 6፣7፡መዝ.72፡2ቆሮ.9
10.1ሳሙ 8-10፡2ቆሮ.10
11.1ሳሙ 11፣12፡1ዜና.1፡2ቆሮ.11
12.1ሳሙ 13፡1ዜና.2፣3፡2ቆሮ.12
13.1ሳሙ 14፡1ዜና.4፡2ቆሮ.13
14.1ሳሙ 15፣16፡1ዜና፡ማቴ.1
15.1ሳሙ 17፡መዝ.9፡ማቴ.2
16.1ሳሙ 18፡1ዜና.6፡መዝ.11፡ማቴ.3
17.1ሳሙ 19፡1ዜና.7፡መዝ.59፡ማቴ.4
18.1ሳሙ 20፣21፡መዝ.34፡ማቴ.5
19.1ሳሙ 22፡መዝ.17፣35፡ማቴ.6
20.1ሳሙ 23፡መዝ.31፣54፡ማቴ.7
21.1ሳሙ 24፡1ዜና.8፡መዝ.57፣58፡ማቴ.8
22.1ሳሙ 25፣26፡1ዜና.25፣26፡መዝ.63፡ማቴ.9
23.1ሳሙ 27፡1ዜና.9 ፡መዝ.141፡ማቴ.10
24.1ሳሙ 28፣29፡መዝ.109፡ማቴ.11
25.1ሳሙ 30፣31፡1ዜና.10፡ማቴ.12
26.2ሳሙ 1፡መዝ.14፡ማቴ.13
27.2ሳሙ 2፡1ዜና.11፡መዝ.142፡ማቴ.14
28.2ሳሙ 3፡1ዜና.12፡ማቴ.15
29.2ሳሙ 4፣5፡መዝ139፡ማቴ.16
30.2ሳሙ 6፡1ዜና.13፡መዝ.68፡ማቴ.17

ጥር
1.1ዜና 14፡መዝ.132፡ማቴ.18
2.1ዜና 15፣16፡ 106፡ማቴ.19
3.2ሳሙ 7፡1ዜና.17፡መዝ.2፡ማቴ.20
4.2ሳሙ 8፣9፡1ዜና18፣19፡ማቴ.21
5.2ሳሙ10፡1ዜና.20፡መዝ10፡ማቴ.22
6.2ሳሙ 11፣12፡መዝ.51፡ማቴ.23
7.2ሳሙ 13፣14፡ማቴ.24
8.2ሳሙ 15፣16፡መዝ.32፡ማቴ.25
9.2ሳሙ 17፡መዝ.72፡ማቴ.26
10.2ሳሙ 18፡መዝ.56፡ማቴ.27
11.2ሳሙ 19፣20፡መዝ.55፡ማቴ.28
12.2ሳሙ 21-23፡ተሰ.1
13.2ሳሙ 24፡1ዜና.21፡መዝ.30፡ተሰ.2
14.1ዜና 22-24፡ተሰ.3
15.1ዜና 25-27፡ተሰ.4

# መጽሐፍ ቅዱስ የማንበቢያ ዕቅድ

## መጽሐፍ ቅዱስን በአንድ ዓመት

•••••••••••••••••••••••••••••

## መጽሐፍ ቅዱስን በአንድ ዓመት

16.1ነገ 1፡1ዜና.28፡መዝ.91፡ተሰ.5
17.1ነገ 2፡1ዜና.29፡መዝ.95፡ተሰ.1
18.1ነገ  3፡2ዜና.1፡መዝ.78፡ተሰ.2
19.1ነገ 4፣5 ፡2ዜና.2፡መዝ.101፡ተሰ.3
20.1ነገ 6፡2ዜና.3፡መዝ.97፡ሮሜ.1
21.1ነገ 7፡2ዜና.4፡መዝ.98፡ሮሜ.2
22.1ነገ 8፡2ዜና.5፡መዝ.99፡ሮሜ.3
23.2ዜና 6፣7፡መዝ.135፡ሮሜ.4
24.1ነገ 9፡2ዜና.8፡መዝ.136፡ሮሜ.5
25.1ነገ 10፣11፡2ዜና.9፡መዝ፡ሮሜ.6
26.ምሳ 1-3፡ሮሜ.7
27.ምሳ 4-6፡ሮሜ.8
28.ምሳ 7-9፡ሮሜ.9
29.ምሳ 10-12፡ሮሜ.10
30.ምሳ 13-15፡ሮሜ.11

የካቲት
1.ምሳ 19-21፡ሮሜ.13
2.ምሳ 22-24፡ሮሜ.14
3.ምሳ 25-27፡ሮሜ.15
4.ምሳ 28፣29፡መዝ.60፡ሮሜ.16
5.ምሳ 30፣31፡መዝ.33፡ኤፌ.1
6.መክ 1-3፡መዝ.45፡ኤፌ.2
7.መክ 4-6፡መዝ.18፡ኤፌ.3
8.መክ 7-9፡ኤፌ.4
9.መክ 10-12፡መዝ.94፡ኤፌ.5
10.መኃልየ 1-4፡ኤፌ.6
11.መኃልየ 5-8፡ፊሊ.1
12.1ነገ 12፡2ዜና.10፣11፡ፊሊ.2
13.1ነገ 13፣14፡2ዜና.12፡ፊሊ.3
14.1ነገ 15፡2ዜና.13፣14፡ፊሊ.4
15.1ነገ 16፡2ዜና.15፣16፡ቆላ.1
16.1ነገ 17-19፡ቆላ.2
17.1ነገ 20፣21፡2ዜና.18፣19፡ቆላ.3
18.1ነገ  22፡2ዜና.18፣19፡ቆላ.4
19.2ነገ 1-3፡መዝ.82፡1ጢሞ.1
20.2ነገ 4፣5፡መዝ.83፡1ጢሞ.2
21.2ነገ 6፣7፡2ዜና.20፡1ጢሞ.3
22.2ነገ 8፣9፡2ዜና.21፡1ጢሞ.4
23.2ነገ 10፡2ዜና.22፣23፡1ጢሞ.5
24.2ነገ 11፣12፡2ዜና.24፡1ጢሞ.6
25.ኢዩ 1-3፡2ጢሞ.1
26.ዮሐ 1-4፡2ጢሞ.2
27.2ነገ 13፣14፡2ዜና.25፡2ጢሞ.3
28.አሞፅ 1-3፡መዝ.80፡2ጢሞ.4
29.አሞፅ 4-6፡መዝ.86፡ቲቶ.1
30.አሞፅ 7-9፡መዝ.104፡ቲቶ.2

መጋቢት
1.ኢሳ 1-3፡መዝ.115፣116፡ቲቶ.3
2.ኢሳ 4፣5፡2ዜና.26፡ይሁዳ
3.ኢሳ 6፣7፡2ዜና.27፡ፊሊሞን
4.2ነገ 15፣16፡ሆሴ.1፡ዕብ1
5.ሆሴ 2-5፡ዕብ.2
6.ሆሴ 6-9፡ዕብ.3
7.ሆሴ 10-12፡መዝ.73፡ዕብ.4
8.ሆሴ 13፣14፡መዝ.100፣102፡ዕብ.5
9.ሚክ 1-4፡ዕብ.6
10.ሚክ 5-7፡ዕብ.7
11.ኢሳ 8-10፡ዕብ.8
12.ኢሳ 11-14፡ዕብ.9
13.ኢሳ 15-18፡ዕብ.10
14.ኢሳ 19-21፡ዕብ.11
15.ኢሳ 22-24፡ዕብ.12
16.ኢሳ 25-28፡ዕብ.13
17.ኢሳ 29-31፡ያቆ.1
18.ኢሳ 32-35፡ያቆ.2
19.2ነገ 17፡2ዜና.28፡መዝ.46፡ያቆ.3
20.2ዜና 29፣31፡ያቆ.4
21.2ነገ 18፣19፡2ዜና.32፡ያቆ.5
22.ኢሳ 36፣37፡መዝ.76፡1ጴጥ.1
23.2ነገ 20፡ኢሳ.38፣39፡መዝ.75፡1ጴጥ.2
24.ኢሳ 40-42፡1ጴጥ.3
25.ኢሳ 43-45፡1ጴጥ.4
26.ኢሳ 46-49፡1ጴጥ.5
27.ኢሳ 50-52፡መዝ.92፡2ጴጥ.1
28.ኢሳ 53-56፡2ጴጥ.2
29.ኢሳ 57-59፡መዝ.102፡2ጴጥ.3

# መጽሐፍ ቅዱስ የማንበቢያ ዕቅድ

## መጽሐፍ ቅዱስን በአንድ ዓመት

••••••••••••••••••••••••••••••

## መጽሐፍ ቅዱስን በአንድ ዓመት

30.ኢሳ 60-62፡ዮሐ.1
ሚያዚያ
1.ኢሳ 65፣66፡መዝ.66፡ዮሐ.3
2.2ነገ 21፡2ዜና.33፡ዮሐ.4
3.ናሆም 1-3፡ዮሐ.5
4.2ነገ 22፡2ዜና.34፡ዮሐ.6
5.2ነገ 23፡2ዜና.35፡ዮሐ.7
6.ዕምባ 1-3፡ዮሐ.8
7.ሶፎ 1-3፡ዮሐ.9
8.ኤር 1፣2፡ዮሐ.10
9.ኤር 3፣4፡ዮሐ.11
10.ኤር 5፣6፡ዮሐ.12
11.ኤር 7-9፡ዮሐ.13
12.ኤር 10-12፡ዮሐ.14
13.ኤር 13-15፡ዮሐ.15
14.ኤር 16፣17፡መዝ.96፡ዮሐ.16
15.ኤር 18-20፡መዝ.91፡ዮሐ.17
16.2ነገ 24፡ኤር22፡መዝ.112፡ዮሐ.18
17.ኤር 23-25፡ዮሐ.19
18.ኤር 26፣35፣36፡ዮሐ.20
19.ኤር 45-47፡መዝ.105፡ዮሐ.21
20.ኤር 48፣49፡መዝ.67፡1ዮሐ.1
21.ኤር 21፣24፣27፡መዝ.118፡1ዮሐ.2
22.ኤር 28-30፡1ዮሐ.3
23.ኤር 31፣32፡1ዮሐ.4
24.ኤር 33፣34፡መዝ.74፡1ዮሐ.5
25.ኤር 37-39፡መዝ.76፡2ዮሐ
26.ኤር 50፣51፡3ዮሐ
27.ኤር 52፡ራዕ.1፡መዝ143፣144
28.ሕዝ 1-3፡ራዕ.2
29.ሕዝ 4-7፡ራዕ.3
30.ሕዝ 8-11፡ራዕ.4

ግንቦት
1.ሕዝ. 15-16፤ መዝ. 70፤ ራዕይ 6
2.ሕዝ 17-19፤ ራዕይ 7
3.ሕዝ 20-21 መዝ. 111 ራዕይ 8
4.ሕዝ 22-24 ራዕይ 9
5.ሕዝ 25-28 ራዕይ 10
6.ሕዝ 29-32 ራዕይ 11
7.2ነገስት 25፤ 2ቆሮ. 36፤ ኤር. 40-41፤ ራዕይ 12
8.ኤር. 42-44፤ መዝ. 48፤ ራዕይ 13
9.ሰቆቃው ኤር. 1-2፤ አብድዩ፤ ራዕይ 14
10.ሰቆው ኤር. 3-5፤ ራዕይ 15
11.ዳን. 1-2፤ ራዕይ 16
12.ዳን. 3-4፤ መዝ. 81፤ ራዕይ 17
13.ሕዝ. 33-35፤ ራዕይ 18
14.ሕዝ. 36-37፤መዝ. 110፤ ራዕይ 19
15.ሕዝ. 38-39፤ መዝ. 145፤ ራዕይ 20
16.ሕዝ 40-41፤ መዝ. 128፤ ራዕይ 21
17.ሕዝ. 42-43፤ ራዕይ 22
18.ሕዝ 45-46፤ ሉቃስ 1
19.ሕዝ. 47-48፤ ሉቃስ 2
20.ዳን. 5-6፤ መዝ. 130፤ ሉቃስ 3
21.ዳን. 7-8፤ መዝ. 137፤ሉቃስ 4
22.ዳን 9-10፤ መዝ. 123፤ ሉቃስ 5
23.ዳን. 11-12፤ ሉቃስ 6
24.ዕዝራ 1፤ መዝ. 84-85፤ ሉቃስ 7
25.ዕዝራ 2-3፤ ሉቃስ 8
26.ዕዝራ 4፤መዝ.113፤127፤ ለቃስ 9
27.ሐጌ 1-2፤ መዝ. 129፤ ሉቃስ 10
28.ዘካርያስ 1-2፤ ሉቃስ 11
29.ዘካርያስ 4-6፤ሉቃስ 12
30.ዘካርያስ 7-9፤ ሉቃስ 13
መጽሐፍ ቅዱስ በምታነብበት ጊዜ፤ እነዚህን ተመልከት
•ስለእግዚአብሔር ምን ያስተምረኛል?
•ስለሰው ምንያተምረኛል?
•ማስወገድ ያለብኝ ኃጥያት አለ?
•መታዘዝ ያለብኝ ትዕዛዝ አለ?
WWW.DAILYTRANSFORMATION.ORG

# መጽሐፍ ቅዱስ የማንበቢያ ዕቅድ
## መጽሐፍ ቅዱስን በአንድ ዓመት
••••••••••••••••••••••••••••••••
## መጽሐፍ ቅዱስን በአንድ ዓመት

ሰኔ
1.ዘካርያስ10-12፤ መዝ. 126፤ ሉቃስ 14
2.ዘካርያስ 13-14፤ መዝ.145፤ ሉቃስ 15
3.ዕዝ.5-6፤ መዝ. 138፤ ሉቃስ 16
4.አስቴር 1-2፤ መዝ. 150፤ ሉቃስ 17
5.አስቴር 3-8፤ ሉቃስ 18
6.አስቴር 9-10፤ ሉቃስ 19
7.ዕዝራ 7-8፤ ሉቃስ 20
8.ዕዝራ 9-10፤ መዝ. 131፤ ሉቃስ 21
9.ነህምያ 1-2፤ መዝ. 133፤ ሉቃስ 22
10.ነህምያ 3-4፤ ሉቃስ 23
11.ነህምያ 5-6፤ መዝ. 146፤ ሉቃስ 24
12.ነህምያ 7-8፤ ሐዋ.ሥ 1
13.ነህምያ 9-10፤ ሐዋ. ሥ. 2
14.ነህምያ 11-12፤ ሐዋ. ሥ. 3
15.ነህምያ 13፤ ሚል. 1-2፤ ሐዋ. ሥ. 4
16.ሚል. 3-4፤ መዝ. 148፤ ሐዋ.ሥ 5
17.ኢዮብ 1-2፤ ሐዋ.ሥ. 6-7
18.ኢዮብ 3-4፤ ሐዋ. ሥ. 8-9
19.ኢዮብ 5፤ መዝ. 108፤ ሐዋ.ሥ.10-11
20.ኢዮብ 6-8፤ ሐዋ. ሥ 12
21.ኢዮብ 9-10፤ ሐዋ.ሥ. 13-14
22.ኢዮብ 11-12፤ ሐዋ.ሥ. 15-16
23.ኢዮብ 13-14፤ ሐዋ.ሥ 17-18
24.ኢዮብ 15፤ሐዋ.ሥ 19-20
25.ኢዮብ 16፤ ሐዋ.ሥ. 21-23
26.ኢዮብ 17፤ ሐዋ.ሥ 24-26
27.ኢዮብ 18፤ መዝ. 114፤ ሐዋ.ሥ 27-28
28.ኢዮብ 19፤ ማር.1-2
29.ኢዮብ 20፤ ማር. 3-4
30.ኢዮብ 21፤ ማር 5-6

ሐምሌ
1.መዝ. 121፤ ማር. 9-10
2.ኢዮብ 23-24፤ ማር. 11-12
3.ኢዮብ 25፤ ማር 13-14
4.ኢዮብ 26-27፤ ማር. 15-16
5.ኢዮብ 28-29፤ ገላትያ 1-2
6.ኢዮብ 30፤ መዝ. 120፤ ገላትያ 3-4
7.ኢዮብ 31-32፤ ገላትያ 5-6
8.ኢዮብ 33፤ 1ቆሮ1-3
9.ኢዮብ 34-35፤ 1ቆሮ 4-6
10.ኢዮብ 36-37፤ 1ቆሮ 7-8
11.መዝ. 122፤ 1ቆሮ 9-10
12.ኢዮብ 37-38፤ 1ቆሮ 12
13.ኢዮብ 39-40፤ 1ቆሮ 13-14
14.መዝ. 149፤ 1ቆሮ 15-16
15.ኢዮብ 41-42፤ 2ቆሮ 1-2
16.2ቆሮ 3-6
17.2ቆ 7-10
18.መዝ. 124፤ 2ቆሮ 11-13
19.ማቴ. 1-4
20.ማቴ. 5-7
21.ማቴ 8-10
22.ማቴ 11-13
23.ማቴ 14-16
24.ማቴ 17-19
25.ማቴ 20-22
26.ማቴ 23-25
27.መዝ. 125፤ ማቴ 26-27
28.ማቴ 28፤ 1ተሰ. 1-3
29.1ተሰ. 4-5፤ 1ተሰ 1-3
30.ሮሜ 1-4

ነሐሴ
1.ሮሜ 5-8
2.ሮሜ 9-12
3.ሮሜ 13-16
4.ኤፌ. 1-4
5.ኤፌ. 5-6፤ መዝ. 119፡1-80
6.ፊሊ. 1-4
7.ቆላ1-4
8.1ጢሞ. 1-4
9.1ጢሞ 5-6፤ ቲቶ 1-3
10.2ጢሞ. 1-4
11.ፊሊሞን 1ዕብ1-4
12.ዕብ 5-8
13.ዕብ 9-10

# መጽሐፍ ቅዱስ የማንበቢያ ዕቅድ

## መጽሐፍ ቅዱስን በአንድ ዓመት

••••••••••••••••••••••••••••••

## መጽሐፍ ቅዱስን በአንድ ዓመት

**14.ዕብ 12-13 ይሁዳ**
**15.ያዕቆብ1-5**
**16.1ጴጥ 1-5**
**17.2ጴጥ1-3፤ ዮሐ1**
**18.ዮሐ. 2-4**
**19.ዮሐ. 5-6**
**20.ዮሐ 7-8**
**21.ዮሐ. 9-12**
**22.ዮሐ. 12-14**
**23.ዮሐ 15-18**
**24.ዮሐ. 19-21**
**25.1ዮሐ 1-5**
**26.መዝ. 117-119፡ 81-176፤ 2ዮሐ፤ 3ዮሐ**
**27.ራዕይ 1-4**
**28.ራዕይ 5-9**
**29.ራዕይ 10-14**
**30.ራዕይ 15-18**

**ጳግሜ**
**1.ሕዝ 12-14፡ራዕ.5**
**2.ምሳ 16-18፡ሮሜ.12**
**3.ራዕይ 19-22**
**4.ኢዮብ 22፤ ማር 7-8**
**5.ኢሳ 63፣64፡መዝ.107፡ዮሐ.2**

**መጽሐፍ ቅዱስ በምታነብበት ጊዜ፤ እነዚህን ተመልከት**
**•ስለእግዚአብሔር ምን ያስተምረኛል?**
**•ስለሰው ምንያተምረኛል?**
**•ማስወገድ ያለብኝ ኃጥያት አለ?**
**•መታዘዝ ያለብኝ ትዕዛዝ አለ?**
**WWW.DAILYTRANSFORMATION.ORG**

DAILY TRANSFORMATION DT DAILY TRANSFORMATION



# ሕብረት

# **ሕብረት፤** በየሳምንቱ መበረታታት

ኢየሱስ ከአማኞች ጋር የፍቅር ሕብረት እንዲኖረን ይፈልጋል(ዮሐንስ 17፡21)። ወደ እርሱ እስክንሄድ ድረስ በሕይወታችን እንድናድግ(1ተሰሎንቄ 5፡11፣ ሮሜ 12፡10፣ ዕብራውያን 3፡13)፣ እንድንስማማ (ማቴዎስ 18፡19-20 )እና እንድንደጋገፍ (ገላትያስ 5፡13፣ ቆላስያስ 6፡2) ይፈልጋል። ጤናማ ሕብረት የኢየሱስ ተከታዮች መሆናችንን ዓለም የሚያቅበት ምልክት ነው(ዮሐንስ 13፡35)።

ጤናማ የመጽፍ ቅዱስ ጥናት ሕብረት የሚከተሉት እሴቶች ይኖሩታል፤

- **እረኝነት፤** (ሐዋርያት ሥራ 20፡28)
- **የመጽፍ ቅዱስ ሥልጣን፤** (2ጢሞትዮስ 3፡16)
- **ሕብረት፤** ማወቅ፣ መታወቅና መረዳት እንችላለን (ሐዋርያት ሥራ 2፡44-47)
- **መስፋፋት፤** ኢየሱስን ለማወቅ የሚፈልጉትን እናካትታለን(ሐዋርያት ሥራ 2፡47)
- **ማፍራት፤** ኢየሱስ ባዘዘው መሰረት ደቀመዛሙርት ለማፍራት ትክክለኛ ቦታ ነው(ዮሐንስ 13፡15፣ 2ጢሞትዮስ 2፡2)።

## በሐዋርያት ሥራ 2፡36-47 ከምትገኘው የጥንቷ ቤተክርስትያን መማር እንችላለን።


**ጥምቀት፡** "ጴጥሮስም፡- ንስሐ ግቡ፤ኃጥያታችሁምይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ።" (ቁ.38)


**ፍቅርምለ፡** "... በሕብረት..." (ቁ. 42)


**የተሰጡ መሪዎች፡** "በሐዋርያትም ትምህርትና በሕብረት እንጀራውንም በመቁረስ በየጸሎቱም ይተጉ ነበር።" (ቁ. 42


**ፍቅር፡** "... በሕብረት..." (ቁ. 42)


**ምግብና የጌታ እራት፡** "... እንጀራውንም በመቁረስ..." (ቁ. 42)


**ጸሎት፡** "...በሕብረት..." (ቁ. 42)


**እጅ መጫን፡** "ነገር ግን በሰው ሁሉ ፍርሃት ሆነ፤ በሐዋርያትም እጅ ብዙ ድንቅና ምልክት ተደረገ" (ቁ.43)(ያዕቆብ 5፡14)


**መስጠት፡** "መሬታቸውና ጥሪታቸውንም እየሸጡ፤ ማንኛውም እንደሚፈልግ ለሁሉ ያካፍሉት ነበር።" (ቁ. 45)


**አምልኮ፡** "... እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ..." (ቁ.47)


**ደቀመዛሙርትን ማፍራት፡** " እዚአብሔርንም እያመሰገኑ በሕዝብ ሁሉ ፊት ሞገስ ነበራቸው ጌታምየሚድኑትን ዕለት ዕለት በእነርሱ ላይ ይጨምር ነበር።" (ቁ.47)

DAILY TRANSFORMATION

# ሕብረት፤ በየሳምንቱ መበረታታት

**መሪነትን ማጋራት፡** የቡድኑ አባላት የባለቤትነት ስሜት እንዲሰማቸው ኃላፊነት ስጣቸው፡፡ ለምሳሌ፡- ምግብ የሚያመጡና የሚደረድሩ ሰዎችን የሚመድብ እንግዳ ተቀባይ ሰው ፤ የጸሎት ርዕሶችንና መልሶቻቸውን የሚመዘግብ የጸሎት መሪ፤ በሕብረት የሚዘመሩ ዝማሬዎችን የሚመርጥ የአምልኮ መሪ መመደብ ትችላለህ፡፡ ሌላ ሰው ደግሞ ሕብረቱ ድጋፍ የሚደርግበትን ሁኔታ ሊያስተባብር ይችላል፡፡  እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ የሕብረቱ አባል ልዩ ልዩ የጸጋ ስጦታ ሰጥቷል፡፡ ስለዚህ ስጦታቸውን እንዲጠቀሙ እድል ስጣቸው፡፡ አስታውስ፤ ዋናው ግብ እያንዳንዱ አባል ልክ እንዳንተ አስተማሪ እንዲሆንና የራሱን ቡድን እንዲቋቁም ማድረግ ነው!

## የስብሰባ አመራር፡

ይህ ሞዴል ሶስት ሶስተኛ፤ 3/3 በመባል ይታወቃል፡፡ አንድ ስብሰባ ሶስት ክፍሎች ሲኖሩት፤ እያንዳንዱ ክፍል እኩል ሰዓት ይወስዳል፡፡ (ለምሳሌ፡- 120 ደቂቃ የሚወስድ ስብሰባ፤ ለእያንዳንዱ ክፍል 40 ደቂቃ ይሰጣል ማለት ነው፡፡)

**« ወደ ኋላ መመልከት** **︽ ወደ ላይ መመልከት** **» ወደፊት መመልከት**

## « ክፍል 1፡ ወደ ኋላ መመልከት

እንጀራ በጋራ እየቆረሳችሁ የሚከተሉትን ማድረግ ትችላላችሁ፤ **ሀ**. ለሌሎች የቡድን አባላት እንክብካቤ ማድረግ፤ **ለ**. በዝማሬ ማምለክ፤ **ሐ.** ኢየሱስን በመከተልና ሰዎችን በማጥመድ አኗያ ያሳዩትን እድገት መጠየቅ፤ **መ**. ከሐዋርያት ሥራ 2፡26-47 አንጻር የቡድንህን ጤናማነት መመርመር



## ︽ ክፍል 2፤ ወደ ላይ መመልከት

ይህ ክፍል የትምህርት ጊዜ ነው፡፡ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ እንዲያነቡ የምናደርግበት ቀላልና ውጤታማ መንገድ አንድ መጽሐፍ ወስዶ በምዕራፍ ማጥናት ነው፡፡ ( የመጀመሪያውን ዘጠኝ ሳምንታት ኢየሱስን መከተል ላይ በሚያተኩሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ጀምሩ፤ 1) ንስሐ ግባ/ እመን- ሉቃስ 19፡1-10፤   2) ተጠመቅ- ሐዋርያት ሥራ 8፡26-39፤ 3) ጸልይ- ማቴዎስ 5፡ 5-15፤ 4) ደቀመዝሙር አፍራ- ዮሐንስ 4፡4-42፤  5) ጽና- ሐዋርያት ሥረራ 5፡27-42፤ 6) ፍቅር- ሉቃስ 10፡25-37 7)የጌታ እራት- ሉቃስ 22፡7-20፤ 8) ስጥ- ማርቆስ 12፡41-44፤ እና 9) ቤተክርስትያን- ሐዋርያት ሥራ 2፡ 36-47፡፡ ስትጨርሱ ወደ ማርቆስ ወንጌል ኑ፡፡ አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ሲጠና የሚከተሉትን 4 ጥያቄዎች መጠየቅና መመለስ አስፈላጊ ነው፡፡ (ቀጥሎ ባሉት ሳምንታዊ የሕብረት ስብሰባዎች ገጽ ላይ ማስታወሻ ያዙ፡፡ ለእያንዳንዱ ሳምንት አንድ ገጽ)

# ሕብረት፤ **በየሳምንቱ መበረታታት**




1) ስለ **<u>እግዚአብሔር</u>** ምን ተማርክ?

2) ስለ **<u>ሰው</u>** ምን ተማርክ?

3) ማስወገድ ያለብህ ኃጥያት አለ?

4) መታዘዝ ያለብህ ትዕዛዝ አለ?

**ማስታወሻ፡**- አዲሱ ማንነታችን ደቀመዛመርቱ " የተማርኩትን እውነት ለማን ላካፍል?" የሚለውን ጥያቄ እንዲጠይቁ ማድረግ ነው፤

## » ክፍል 3፤ **ወደ ፊት መመልከት**

ሀ. ያስተማርከውን ትምህርት ተማሪዎቹ ሁለት ሁለት እየሆኑ ወይም ደግሞ ጊዜ ካለ ሙሉ ቡድኑ በተግባር እንዲለማመዱ አድርግ።

ለ. እንዴት እንዲታዘዙት እንደሚፈልግ እግዚአብሔርን በጸሎት ጠይቀው የሚለውንም ለመስማት በጸጥታ ጊዜ ውሰድ። አባላት ግባቸውን እንዲያካፍሉ አድርግ። በሚቀጥለው ስብስባ፤ ፈቃደኛ የሆኑ አባላት ያሳዩትን ዕድገት ሊያካፍሉ ይችላሉ።



# ሰምንታዊ
# የሕብረት ጊዜ ገጾች

..............

## ወደ ኋላ መመልከት፤

ያለፈውን ሳምንት ግብ ተግባራዊ ያደረኩበት መንገድ፤

የቡድን ራዕይ፤ ቡድናችን ጤናማ እንዲሆን ከ10ሩ ጉዳዮች የትኛው ላይ ነው ማተኮር ያለብን?



## ወደ ላይ መመልከት፤

በተለየ ሁኔታ የተናረኝ ቃል የቱ ነው? ለምን? ጥያቄ የፈጠረብኝስ ቃል አለ?

- ስለ እግዚአብሔር ምን ተማርኩ?
- ስለ ሰው ምን ተማርኩ?
- ማስወገድ ያለብኝ ኃጥያት አለ?
- መታዘዘስ ያለብኝ ነገር አለ?

## ወደ ፊት መመልከት፤

እግዚአብሔር ምን እንድታደርግ እየጠየቀህ ነው?

ይህንን እውነት ለማን ላካፍል?



# ግለጽ

# ግለጽ፡ የእግዚአብሔርን ፍቅር ማካፈል

የእግዚአብሔርን ምህረት ስታውቅና እንደሚያስፈልግህ ስትረዳ ይህንን ተስፋ ለሌሎች ለማካፈል ያለህ ፍለጎት ሁልጊዜ ትኩስ ይሆናል። ኢየሱስ የመጀመሪያ አፍቃሪህ መሆን እና ለሌሎች ስለእርሱ እንድታወራ ይፈልጋል።

"እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራ ጋር ያስታርቅ ነበርና፤ በደላቸውን አይቆጥርባቸውም ነበር፤ በእኛም የማስታረቅ ቃል አኖረ። እንግዲህ እግዚአብሔር በእኛ እንደሚማልድ ስለ ክርስቶስ መልዕክተኞች ነን፤ ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን ስለ ክርስቶስ እንለምናለን። **2ቆሮንቶስ 5፡ 19-20**

## የክርስቶስ መልዕክት ሁለት ክፍሎች

**ልዩ ክፍል፤ የአንተ ታሪክ:** ከኢየሱስ ጋር የተገናኘሁበት ታሪክ፤ ሁለት ምሳሌዎች፡-

- **ንጉስ ዳዊት፡** "እዚአብሔን የምትፈሩ ሁሉ፤ ኑ፤ ስሙኝ፤ ለነፍሴ ያደረገላትን ልንገራችሁ።" መዝሙር 66፡16

- **ሰማርያዊቷ ሴት፡** "ሴቲቱም፡- ያደረግሁትን ሁሉ ነገረኝ ብላ ስለመሰከረችው ቃል ከዚያች ከተማ የሰማርያ ሰዎች ብዙ አመኑበት።" ዮሐንስ 4:39

የአንተ ታሪክ በ2 እና 3 ደቂቃ ውስጥ የሚከተሉትን ያካትታል፤

1. ጌታን ከማግኘትህ በፊት የነበረህ ሕይወት ምን እንደሚመስል እና ኢየሱስ እንደሚያስፈልግህ እንዴት

ልታውቅ እንደቻልክ ______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

2. ሕይወትህን ለጌታ እዴት እንደሰጠህ ______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

3. ጌታ በሕይወትህ ያመጣው ልዩነት______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

DAILY TRANSFORMATION

# ሰፊው ክፍል፡ የምሥራቹ ቃል

## አንድ ሰው እንዴት የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታይ እንደሚሆን ማስረዳት

ሀ. ሶስት ክቦች፤ ጓደኛህን ስዕል የምትስልበት ወረቀት እንዲሰጥህ ጠይቀው።ስትጨርስ መልሰህ ትሰጠዋለህ፡.




1) ስንጥቅ ያለው ክብ መጀመሪያ ሳል። ይሄ የተሰበረውን ዓለም ይወክላል። በሽታ ፣ አደጋ፣ የተበላሹ ግንኙነቶች። እያንዳንዱ ዚግዛግ መስመር ከዚህ ችግር ራሳችንን ለማዳን የምናደርገውን ጥረት ይወክላል ( ሥራ፣ ቤተሰብ፣ ሱስ፣ ጾታዊ ግንኙነቶች...) ግን የትኛውም የኛ መፍትሔ ዘላቂ አይደለም።

2) የልብ ቅርጽ ውስጡ ያለበት ሁለተኛ ስዕል ሳል። ይህ፤ እግዚአብሔር ለእኛ ያለው ዕቅድ ነው። እግዚአብሔር ዓለምን የሰራው ከእኛ ጋር ሕብረት የሚያደርግበት ቦታ እንዲሆን ነበር። እንደሚወደን እና ይቅር እንደሚለን እናውቃለን። ፍጥረት እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር የገለጸበት ውብ ስጦታ ነው። ነገር ግን፤ ኃጥያት ( ቋሚ መስመር ሳል) የእግዚአብሔርን ዕቅድ እንዳንለማመድ እንቅፋት ሆነ።

3) መሐል ላይ መስቀል ያለው ሶስተኛ ስዕል ሳል። እግዚአብሔር ይወደናል፤ ከእርሱ ጋር ያለን ግንኙነት እዲታደስ ይፈልጋል። ኢየሱስ ወደ ምድር ወረደ (የተዘቀዘቀ ቀስት ሳል)፣ ቃል እንደገባው በመስቀል ላይ ሞቶ በሶስተኛው ቀን ተነሣ (ወደ ላይ የሚያመለክት ቀስት ሳል)። ተሐድሶ እና ይቅርታ፤ ኢየሱስን የሕይወታችን ንጉስ (ዘውድ ሳል) እንድናደርገው ይጠይቀናል። እንዴት ነው ንጉስ የምናደርገው? "መመለስና ማመን " አለብን። (እዚነህን ቃላት በስዕሉ ላይ ጻፍ) (ሮሜ፡ 10፡9፣10) የተንበረከከ ሰው ስዕል ሳል።

4) ጓደኛህን፤ የትኛው ስዕል እንደሚገልጸው ጠይቀው። ስብራት ወይስ የእግዚአብሔር ፍቅር ? ከራስ አገዛዝ ወደ እግዚአብሔር አመራር እንዲሁም ከኃጥያት ወደ እግዚአብሔር እቅድ የመመለስ ጸሎት እንዲጸልዩ ጋብዛቸው (ጸሎት፤ኃጥያተኛነትን ማመንና ይቅርታን መጠየቅ፣ኢየሱስ አምላክ መሆኑንና ለኃጥያቴን እዳ ለመክፈል መሞቱን ማመን እና አምላኬ ነህ ብሎ በአፍ መመስከር)

5) ለጓደኛህ ስለአዲሱ ማንነቱ አስረዳው፤ 2ቆሮንቶስ 5፡17-21 አዲስ ፍጥረት መሆኑን ይናገራል (የሚንጸባርቅ ብርሃንን የሚያመለክቱ መስመሮች የተከበበ ሰው ሳል)። ቤተሰቡ እና ጓደኞቹ ከውድቀት ወደ ምህረት ህይወት እንዲመጡ የሚረዳ የኢየሱስ አምባሳደር እንደሆነ ይህ ክፍል ይናገራል። (በእግዚአብሔር እቅድ እና በውድቀት መካከል ድልድይ የሚሆን መስመር ሳል)።

6) የበለጠ እንዲያውቅ አንተ ወደምትካፈልበት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድን ይዘኸው ሂድ።

7) ክብ ስዕል ሳልና ጓደኛህ ይህንን ስዕል የሚያካፍሏቸውን አምስት የቅርብ ቤተሰቡንና ጓደኞቹን ስም በክቡ ውስጥ እንዲጽፍ ጠይቀው። (የሚከተለውን ምሳሌ ተመልከት)

# ሰፊው ክፍል፡ የምሥራቹ ቃል

የሚከተለው ስዕል ለናሙና የቀረበ የኦይኮስ ክብ ነው። በመሃከለኛው ክብ የራስህን ስም አስገባ። በመቀጠል ስለኢየሱስ ያልሰሙ አምስት የቅርብህ ሰዎችን ከዙሪያ ባሉት ክቦች ውስጥ አስፍር።




ለ. **የሮሜ መንገድ፤** ንሰሃ መግባት እና ኢየሱስን የመከተልን አስፈላጊነት ለሰው የምናሳይት መንድ ነው፡ ፡ (የሚከተሉትን ጥቅሶች ቶሎ ለማግኘት ጥቅሶቹ ያሉበትን ገጽ መጽሐፍ ቅዱስህ ላይ ምልክት ማድረግ ትችላለህ።) የመጀመሪያው ጥቅስ፤ (ሮሜ 3፡23፣ ገጽ -----) በፊት ገጽ የውስጠኛው ክፍል ላይ ይጻፋል።

• **ሮሜ 3፡23 (ሁሉ ኃጥያትን ሠርተዋል)** "ሁሉ ኃጥያት ሠርተዋልና የእግኢዘብሐየርም ክብር ጎድሏቸዋል።"

**ሮሜ 6፡23 (የኃጥያት ዋጋ)** "የኃጥያት ደመወዝ ሞት ነውና፤ የእግዚአብሔ የጸጋ ስጦታ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን የዘላለም ሕይወት ነው።"

**ሮሜ 5፡8 (ክርስቶስ እዳችንን ከፍሏል)** "ነገር ግን ገና ኃጥያተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል።"

**ሮሜ 10፡-9፣10 (በእምነት መዳን)** "ኢየሱስ ጌታ እደሆነ በአፍህ ብትመሰክር እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህ። ሰው በልቡ አምኖ ይጸድቃልና በአፉም መስክሮ ይድናልና።"

የማካፈል ዝርዝር፡ በሚቀጥለው ገጽ ስለኢየሱስ እየነገርካቸው ያሉ ሰዎችን ስም ዝርዝር የምትጽፍበትን ቦታ አዘጋጅተናል። የቅርብ ግንኙነት ካለህ ሰዎች እንድትጀምር እናበረታታለን ወይም (ኦይኮስ፤ በግሪክ ቤተሰብ ማለት ነው)። በዙሪያህ ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም እንደሌላቸው የሚሳስብህ ሰዎች እነማናቸው? ስማቸውን ዘርዝር። እግዚአብሔር ልባውን ለመስማት እንዲያዘጋጅ ጸልይ። በመጀመሪያ የመሰከርክላቸውን ቀን ጻፍ። ሕይወታቸውን ለጌታ ከሰጡ ጌታን የተቀበሉበትንና የተጠመቁበትን ቀን መዝግብ። በመጨረሻ፤ የህይወቴ ማስታወሻን በጋራ በመለማመድ በታማኝነት ጌታን እንዲከተሉ አስተምራቸው። ስትጀምሩ ቀኑን መመዝገብ አትርሳ።

# ሰፊው ክፍል፡ የምሥራቹ ቃል

| ስም | ማካፈል | መቀበል | ጥምቀት | ሕይወት |
| --- | --- | --- | --- | --- |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |

DAILY TRANSFORMATION DT DAILY TRANSFORMATION

# የመንፈሳዊ ዕድገት ዳሰሳ

• • • • • • • • • • • • • •

**ስም** ________________________________________________

**ኢሜል** ________________________________________________

**ስልክ** ________________________________________________

ይህንን ዳሰሳ የወሰድኩበት ቀን፡ _______/ _______/ _________(

- ☐ የሕይወቴ ማስታወሻን ለመጻፍ ቃል የገባሁበት ቀን
- ☐ ከአንድ ወር በኋላ
- ☐ ከ90 ቀናት በኋላ
- ☐ 1ኛ ዓመት በዓል

ባለፈው ወር...

• የአምልኮ ፕሮግራሞችን ምን ያህል ጊዜተካፈልክ? ( መልሱን አክብብ) 0 1 2 3 4+ ______

• ከእግዚአብሔር ጋር ያሳለፍከው የጸሎት ጊዜ ምን ያህል የጠበቀ ነበር? 1(ቀዝቃዛ) -10 (ሕይወት ሰጪ) ______

• በሳምንት መጽሐፍ ቅዱስህን ምን ያህል ጊዜ አንብበሃል? (መልሱን አክብብ) 0 1 2 3 4 5 6 7 ______

• መጽሐፍ ቅዱስ በምታነብት ወቅት ማስታወሻ መያዝ የየዕለት ልምድህ ሆኗል? (አንዱን አክብብ) አዎ አይደለም ______

• ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና ለህብረት ከሌሎች አማኞች ጋር በየምን ያሉ ጊዜ ተገናኘህ? (አንዱን አክብብ) 0 1 2 3 4+ ______

• የኢየሱስን ወንጌል ለምን ያህል ሰዎች አካፈልክ? (አንዱን አክብብ) 0 1 2 3 4 5 6 7 8 9 10+ ______

**የሚከተሉት 14 ነጥቦች ህይወትህን ምን ያህል ይገልጻሉ?** 1 (እምብዛም አይገልጽም) -10(እጅግ ይልጻል)

1. እግዚአብሔርን በጥልቀት ለማወቅ እፈልጋለሁ። (ፊሊ. 3፡7-11, መዝ. 42፡1፤ 63፡1) ______
2. ከባድና መከራ የሚስከትል እንኳን ቢሆን የእግዚአብሔርን እውነት በሀሴት እቀበላለሁ። (ሐዋ.14፡22) ______
3. እግዚአብሔር ከብሮ ማየት ስለምፈልግ አገለግለዋሁ።(ቆላ. 3፡17, 1ቆሮ. 10፡31) ______
4. ስጸልይና ቃን ሳነብ ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀ ህብረት አደርጋለሁ።( 1ጴጥ. 2፡1, ቆላ. 2፡6-7) ______
5. በእግዚአብሐየር ቃልና በአስተምህሮ እውቀት እያደግሁ ነው። 2ጳጥ 3፡16, ዕብ. 5፡11-14) ______
6. ከሌሎች ክርስትያኖች ጋር የፍቅር ህብረት አለኝ፤ እንዲሁም አገለግላቸዋለሁ።(1 ተሰ.5፡11, 1ዮሐ.4፡7) ______
7. ከቤተሰቦቼ ጋር ባለኝ ግንኙነት ጌታን አሳያለሁ። (ቆላስያስ 3፡18-21) ______
8. የኢየሱስን ጸጋ፣ ፍቅርና እውነት ለቤተሰቦቼ፣ ጎረቤቶቼ እና ከዚያም ባሻገር አካፍላለሁ።(ቆላስያስ 4፡3-6 ______
9. ከኃጥያት ጋር ብርቱ ጦርነት አደርጋለሁ። (ቆላስስ 3፡5) ______
10. በቅርቤ ያሉ ሰዎች ኢየሱን በመምሰል እያደግሁ እንደሆነ ይነግሩኛል።(ገላትያ 5፡22-23) ______
11. መንፈስ ቅዱስ እንዳገለግልና የኢየሱስን መንግስት እንድገልጽ እየረዳኝ ነው።ሉቃስ 10፡9, ሐዋ. ሥ. 1፡8) ______
12. ስለኢየሱስ ወንጌል ከነገርኳቸው በኋላ ሰዎች ኢየሱስን ለመከተል እየወሰኑ ነው።(ሐዋ. ሥ. 2፡41) ______
13. ስለ ክርስቶስ ላካፈልኳቸው ሰዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድን እየመሰረትኩ ነው። (ዕብ. 10፡24-25) ______
14. ስለ ኢየሱስ እንዲያካፍሉና የራሳቸውን የመጽፍ ቅዱስ ጥናት ቡድን እንዲመሰርቱ ሌሎችን እያሰለጠንኩ ነው፡ ፡ (ምሳሌ 14፡4, ሐዋ. ሥ. 14፡21-23) ______

የዚህን ዳሰሳ ውጤት ለአሰልጣኝህ ወይም ለ survey@dailytransformation.org ኢሜይል እንድታደርግ እንጠይቃለን።